| | |
|---|---|
| **መመሪያ ቁጥር 01/2000**<br>**የአካባቢ ደረጃዎችን ለማጽደቅ የወጣ መመሪያ** | **DIRECTIVE NO.01/ 2008**<br>**A DIRECTIVE ISSUED TO APPROVE ENVIRONMENTAL STANDARDS** |
| የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 አንቀጽ 6 መሠረት የአካባቢ ደረጃዎችን የወሰነ በመሆኑ፣ | **WHEREAS,** the Environmental Protection Authority has, according to Article 6 of the Environmental Pollution Control Proclamation No 300/2002, set environmental standards; |
| የአካባቢ ምክር ቤት -----2000 ዓ.ም. ባካሄደው የመጀመሪያ መደበኛ ስብሰባ የአካባቢ ደረጃዎቹን የተቀበላቸው በመሆኑ ፣ | **WHEREAS,** the Environmental Council has accepted the Environmental Standards at its 1st ordinary session held on-----------2008; |
| በአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 295/1995 አንቀጽ 6 (7) መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል:: | **THEREFORE,** this directive is issued according to Article 9(3) of the Environmental Protection Organs Establishment Proclamation No. 295/2002. |
| 1. <u>ሥያሜ</u><br>ይህ መመሪያ "የአካባቢ ደረጃዎች ማፅደቂያ መመሪያ ቁጥር 01/2000" ተብሎ ሊጠራ ይችላል:: | **1. Designation**<br>This directive may be cited as '' Directive No. 01/ 2008 for the Approval of Environmental Standards" |
| 2. <u>የደረጃዎች መጽደቅ</u><br>ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዘው የሚገኙት የአካባቢ ደረጃዎች ፀድቀዋል:: | **2. Approval of the Standards**<br>The Environmental Standards attached hereto are hereby approved. |
| 3. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u><br>ይህ መመሪያ ከ---- ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል:: | **3. Effective Date**<br>This directive shall enter into force as of the---- day of 2008. |
| አዲስ አበባ ---- ቀን 2000 ዓ.ም.<br>መለስ ዜናዊ<br>የአካባቢ ምክር ቤት ሰብሳቢ | Done at Addis Ababa, this ---- day of ------- 2008.<br>Meles Zenawi<br>Chairperson of the Environmental Council |

| | |
|---|---|
| **መመሪያ ቁጥር 02/2000**<br>**የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያና መቆጣጠሪያ ደንብ ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን የኢንዱስትሪ መስኮች ለመወሰን የወጣ መመሪያ** | **DIRECTIVE NO.02/ 2008**<br>**A DIRECTIVE ISSUED TO DETERMINE INDUSTRIAL ENTERPRISES SUBJECT TO THE INDUSTRIAL POLLUTION PREVENTION AND CONTROL REGULATIONS No. --/ 2008** |
| የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያና መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር ---/2000 ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ኢንዱስትሪዎች መለየት አስፈላጊ በመሆኑ፣ | **WHEREAS,** it is essential to enlist the category of industrial enterprises subject to the Industrial Pollution Prevention and Control Regulations No. ---/ 2008, |
| የአካባቢ ምክር ቤት፣ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 3 በተዘረዘሩት ኢንዱስትሪዎች ላይ የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያና መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር ---/2000 ተፈፃሚ እንዲሆን የተስማማ ስለሆነ፣ | **WHEREAS,** the Environmental Council has agreed upon the industrial enterprises listed under article 3 of this Directive to be subject to the Industrial Pollution Prevention and Control Regulations No. ---/ 2008; |
| በአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 295/1995 አንቀጽ 9 (3) መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል:: | **THEREFORE,** this directive is issued in accordance with Article 9(3) of the Environmental Protection Organs Establishment Proclamation No. 295/2002. |
| 1. <u>ሥያሜ</u><br>ይህ መመሪያ "የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያና መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር ---/2000 ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ኢንዱስትሪዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 02/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል:: | **1. Designation**<br>This directive may be cited as the "Directive No. 02/ 2008 issued to determine the Categories of industrial enterprises subject to the Industrial Pollutions Prevention and Control Regulations No. . ---/ 2008 " |
| 2. <u>ደንቡ የሚመለከታቸው ኢንዱስትሪዎችን ስለመወሰን</u> | **2. Determination of Industrial enterprises subject to the Regulations** |
| 1. የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያና መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር --/2000፣ በጨርቃ ጨርቅ፣ በቆዳ፣ በኬሚካል፣ በስኳር፣ በሲሚንቶ፣ በብረታ ብረት እንዲሁም በምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል:: | 1.The Industrial Pollutions Prevention and Control Regulations No. ---/ 2008 is applicable on textile, leather, chemical, sugar, cement, metal and food and beverage industrial enterprises. |
| 2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተመለከተው የኢንዱስትሪዎች ዝርዝር ሊሻሻል ይችላል:: | 2.The list of industrial enterprises specified under subarticle 1 of this article may be modified. |

| | |
|---|---|
| 3. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u><br>ይህ መመሪያ ከ---- ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡<br><br>አዲስ አበባ ---- ቀን 2000 ዓ.ም.<br>መለስ ዜናዊ<br>የአካባቢ ምክር ቤት ሰብሳቢ | **3. Effective Date**<br>This directive shall enter into force as of the---- day of 2008.<br><br>Done at Addis Ababa, this ---- day of ------- 2008.<br>Meles Zenawi<br>Chairperson of the Environmental Council |